

# ~ 17 ~

# ከፋው በደግ ሲለወጥ

17-1

ዮሴፍ የተወለደው ያዕቆብ በጣም ከሚወዳት ሚስቱ ነው። በዚህ ምክንያት ዮሴፍ በአባቱ ዘንድ ከሌሎች ልጆቹ ሁሉ በጣም የተወደደ ነበር። ስለሆነም ለዮሴፍ ከሌሎች ልጆቹ ሁሉ የተለየ በጎ ነገር ያደርግለት ነበር። እርግጥ ነው ዮሴፍ በተፈጥሮው ንቁና ብዙ ተሰጥኦ ያለው ልጅ ነበር። ያዕቆብም ዮሴፍ የተለየ የተፈጥሮ ስጦታዎች ያለው ልጅ እንደነበረ አስቀድሞ አውቋል። ይሄም ሌላው ምክንያት ነው ያዕቆብ ለዮሴፍ ልዩ ፍቅር እንዲኖረው ያደረገው። ያዕቆብ ልጁን ዮሴፍን በጣም መውደዱ ጥፋት የለበትም። ጥፋቱ ግን ከልጆቹ ሁሉ ይበልጥ እንደሚወደው ለዮሴፍና ለሌሎች ልጆቹ ማሳወቁ ነበር። ቤተሰቡ በሞላ ዮሴፍ ያዕቆብ ተወዳጅ ልጁ እንደነበረ ያውቅ ነበር። በዚህ ምክንያት ዮሴፍ በመሞላቀቅ ያደገ ልጅ ነበር። ያዕቆብም ለዮሴፍ ያደላ እንደነበር በግልጽ ይታይ ነበር። ማድላቱንም ልጆቹ ሁሉ በግልጽ ያወቁት ለዮሴፍ በልዩ ልዩ ቀለም ያሸበረቀ ኮት ገዝቶ በሰጠው ጊዜ ነው። ይህ ልብስ ከወንድሞቹ ሁሉ የተለየ አደረገው። ያም የበለጠ መጠላትን በዮሴፍ ላይ እንዲደርስበት አደረገ።

## ዮሴፍ ተወዳጅ በመሆኑ ጠላት አፈራ

አባትዬው ይህን ሲያደርግ ለዮሴፍ በጎ ማሰቡ ነው። ይሁን እንጂ ይበልጥ ዮሴፍ እንዲጠላ አደረገው። ያዕቆብ ይህንን ሲያደርግ ለዮሴፍ በጎ ማሰቡ ነበር። ነገር ግን መልካሙ ወደ ክፉነት ተለወጠ። ሌላው ትልቁ ችግር ደግሞ ዮሴፍ እራሱ ነበር። አባቱ ከሌሎች ልጆቹ የበለጠ እንደሚወደው ስላወቀ በልቡ ተኩራራ። ስለራሱም በማሰብ ሰከረ። ሁኔታው በሞላ ተለወጠ። እራሱንም ከሌሎች ልጆች በበለጠ አድርጎ መመልከት ጀመረ። ስለራሱ ያየው ሕልም በእርሱ ዘንድ ብቻ ታውቆ የቀረ ሳይሆን ለወንድሞቹም ስለነገራቸው ወንድሞቹ ያንን በደስታ መቀበል አልፈለጉም። ዮሴፍ አንድ ቀን ሕልም አይቶ ለወንድሞቹ ነገራቸው። እኔ ያለምኩትን ሕልም ስሙ "እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበርና እነሆም የኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተም ነዶዎች በዙሪያ ከበው እነሆ ለእኔ ነዶ ሰገዱ" (ዘፍ. 37፥6 ና 7)። ወንድሞቹም ሕልሙን ካዳመጡ በኋላ "እንዴ! ይህ ሕልምህ ምንድነው? በእኛ ልትነግሥ ይሆን ወይስ እኛን ልትገዛን ይሆን?" አሉት። በዚህም ምክንያት የበለጠ ጠሉት። ደግሞ ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወንድሞቹም እንዲህ ሲል ነገራቸው። እነሆ ሌላ ሕልምን አለምኩ፤ "እነሆ ጸሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ" ለአባቱና ለወንድሞቹም ነገራቸው። አባቱም ሲሰማ ገለጸው "ይህ ያለምከው ሕልም ምንድነው? በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?" (ዘፍ. 37፥9-10)።

# ዮሴፍ ያልጠበቀው ደረሰበት

ዮሴፍ የ17 ዓመት ወጣት በነበረበት ጊዜ አንድ ቀን አባቱ በተራራ ላይ ሆነው ከብቶቻቸውን ያግዱ ወደነበሩት ወንድሞቹ ላከው። ወንድሞቹም ከሩቅ ዮሴፍ ሲመጣ አዩት። እርሱ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ተማከሩ። “ያ ባለ ሕልሙ ዥጉርጉር ልብሱን ለብሶ እየመጣ ነው፤ እንግዲህ ይህን አይነት እድል አጋጥሞናልና ጊዜው ዛሬ ነው” ብለው ወሰኑ። ልክ አጠገባቸው እንደደረሰም እንቅ አድርገው በመያዝ የሚያምረውን ዥጉርጉር ልብሱን በመቅደድ ደበደቡት። ዮሴፍን በመደብደብ ብቻ ሳያወሰኑ ቀጥለውም ቆሻሻ ጉድጓድ ውስጥ ከተቱት። በዚህ ጊዜ  ውስጥ ዮሴፍ ቀደም ሲል በሕልም ያየው አንደኛውም ነዶ አልሰገደለትም፤ ወይንም ከሰማይ ከዋክብቶች አንዳቸውም አልተኀበሱለትም። ይሁዳ ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው “ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሸሽግ ጥቅማችን ምንድነው? ለእስማኤላውያን እንሸጠው፤ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አንጣል፤ ወንድማችን ሥጋችንም ነውና” (ዘፍ 37፥26-27)። እነርሱም ዮሴፍን ከጣሉበት ጉድጓድ አውጥተው ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በ20 ብር ሸጡት። እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብጽ ይዘውት ሄዱ። ወንድሞቹም ይህንን ሲያደርጉ ከእንግዲህ ወዲያ በዮሴፍ ምክንያት ምንም ዓይነት ችግር እንደማይመጣባቸው ገምተው ነበር። ቢሆንም የዮሴፍ ሕይወት በዚህ ላይ አላበቃም። ይህ የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልነበረም። እነዚህ ጨካኝ ወንድሞቹ “ወረወርነው” ሲሉ እግዚአብሐር ደግሞ ሁኔታውን ለውጦ አነሳው። “አዋረድነው” ሲሉ እግዚአብሔር ከፍ አደረገው። “አጠፋነው” ሲል እግዚአብሔር አበዛው። ዮሴፍ ከፉው ወደ ደግ እንዴት ሊለወጥለት ቻለ? ከማጣት ወደ ማግኘት፣ ከመሸነፍ ወደ ማሸነፍ፣ ከጥፋት ወደ ሕይወት መሸጋገር የቻለበት ዋናው ምስጢሩ ምን ይሆን? እኛም የተለያየ ሁኔታ ስለሚያጋጥመን፥ ከዮሴፍ መማር ያስፈልገናል። አንዳንድ ጊዜ የሚደርስብን ግጭት ወይም ግፊት ከባድ ስለሆነ ገፍቶ በጉልበታችን ያንበረክከናል። ታዲያ በዚህ ግፊት ላይ እንዴት በጎ ነገር ልናገኝበትና ልናወጣበት እንችላለን?

# ክፉው ሁሉ ለበጎ አይደለም

ይህንን ለማወቅ በጥንቃቄ የዮሴፍን ሕይወት መመርመር ያስፈልገናል። በሕይወታችን ውስጥ ያጋጠሙን ነገሮች ሁሉ ለበጎ የሆኑ አይደሉም። በዓለም ውስጥ ብዙ በጎ የማይሆኑ የተለያዩ መጥፎ ነገሮች ይደርሳሉ። ዮሴፍ ድልን ያገኘው መከራ ስላጋጠመው ብቻ አይደለም። ወይንም ዮሴፍ ሊያሸንፍ የቻለው በአካባቢው መልካም እድል ስላጋጠመው አይደለም። የአካባቢ ሁኔታ እርግጥ ነው ሁኔታችንን ቅርጽ ሊያወጣ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ የአካባቢ ሁኔታ ብቻ ለማደግ ወይም ደግሞ ለማነስ ምክያት አይሆንም። ሁለት ዓይነት ሰዎች በአንድ ዓይነት አካባቢ ሁኔታ ውስጥ ቢያልፉ፥ የአካባቢው ሁኔታው ምንም ያህል አስከፊ ቢሆንም አንደኛም የማደግና ከፍ የማለት አቅጣጫ ይይዛል። ሁለተኛው ግን የአካባቢ ሁኔታ አሰነካክሎት ሊወድቅ ይችላል።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**